የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ነሐሴ ፰ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.58
ADDIS ABABA 14th August, 2024


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፬/፪ሺ፲፮

የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ……… ………………………………………ገጽ ፲፭ሺ፱፻፲፫


## Content


Proclamation No. 1324/2024

Rural Land Administration and Use Proclamation ……....................................................Page 15913


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፬/፪ሺ፲፮

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ**

የአርሶ አደሩን፣ ከፊል አርብቶ አደርና የአርብቶ አደሩን የኑሮ ደረጃ አገሪቱ ከደረሰችበት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ እድገት ጋር ለማራመድ እንዲቻል እንዲሁም አርሶ አደሩን፣ ከፊል አርብቶ አደሩና አርብቶ አደሩን በመሬት ይዞታው ላይ ያለውን የንብረት መብት ለማጠናከር የተሻሻለ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የከፊል አርብቶ አደርና የአርብቶ አደሩ ባህላዊ የመሬት አጠቃቀም እና አጠባበቅ ሥርዓት ጠቃሚና ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው ስለሆነ እና ኢትዮጵያ የአርብቶ አደሮች የመሬት ይዞታ መብት በተመለከተ በህገ-መንግስቱ እውቅና የተሰጠው በመሆኑ፤ እና በዓለም አቀፍና በአህጉር ደረጃ የፈረመቻቸውን ስምምነቶች ተግባራዊ ለማድረግ እና በማስፈፀሚያ ሕግ ማስደገፍ በማስፈለጉ፤

የገጠር መሬት ምዝገባ መረጃን ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ለማደራጀትና ለተጠቃሚው በአግባቡ ለማሰራጨት የሚያስችል ምቹ የሕግ ማዕቀፍ በመፍጠር የባለይዞታዎችን የይዞታ ዋስትናን በማጠናከር በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እና አጠቃቀም ላይ ጉልህ ለውጥ ለማምጣት፣ በመሬት ላይ የሚነሱ ግጭቶችን ለመቀነስ፣ እና መንግስት እና ተጠቃሚዎች አስተማማኝ የሆነ መረጃ የሚያገኙበትን ዘመናዊ የመሬት መረጃ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

## PROCLAMATION NO. 1324/2024

**FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA RURAL LANDS ADMINISTRATION AND USE PROCLAMATION**

**WHEREAS**, it has become necessary to improve the livelihood of farmers, semi-pastoralists, and pastoralists at the level of the Country's economic, political, and social development by establishing improved rural land administration and use system that enhance the land property rights of farmers, semi-pastoralists, and pastoralists over their landholding;

**WHEREAS**, it has been proved that the customary land use and land management of semi-pastoralists and pastoralists have significant and noticeable importance; and the landholding rights of these groups are recognized under the FDRE Constitution, and it has become necessary to issue laws that implement international and regional treaties to which Ethiopia is signatory;

**WHEREAS**, it has become necessary to establish a modern land information system that provides reliable data to users in order to bring about significant change in natural resource use and conservation practices by strengthening tenure security of landholders; and reduce land related disputes;


ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

የተለያዩ የሀገሪቱ የሥነ ምህዳር ቀጠናዎችን ያገናዘበ ዘላቂ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ በማውጣትና በመተግበር የተፈጥሮ ሀብቶችን በዘላቂነት በመጠበቅና በማልማት ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ በማስፈለጉ፣፤

የሴቶች እና ድጋፍ የሚሹ ሰዎችን የመሬት ተጠቃሚነት መብት የሚያረጋግጥና የሚያጠናክር የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካታች ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፪) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ</u>**

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፬/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "የገጠር መሬት" ከማዘጋጃ ቤት ክልል ውጭ ወይም አግባብ ባለው ሕግ ከተማ ተብሎ ከሚሰየመው ውጭ ያለ ማንኛውም መሬት ነው፤

፪/ "የገጠር መሬት መረጃ ሥርዓት" ማለት የገጠር መሬት እና መሬት ነክ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ በመተንተንና በአግባቡ እንዲያዙና ወቅታዊ በማድረግ ለተጠቃሚዎች የማሰራጨት ሥርዓት ነው፤

፫/ "የገጠር መሬት ምዝገባ" ማለት በገጠር መሬት የመጠቀም መብትና ባለይዞታነት የሚገለፅበት የመረጃ ማሰባሰብ፣ የማጠናቀርና ወቅታዊ የሚደረጉበት ሂደት ነው፤

፬/ "የገጠር መሬት አስተዳደር" ማለት የገጠር መሬት ይዞታ መብት የሚሰጥበት፣ ዋስትና የሚረጋገጥበት፣ የመሬት ሀብት ዋጋ የሚተመንበት፣ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሚተገበርበት በመሬት ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ ግጭቶች የሚፈቱበትና ግዴታዎች የሚተገበሩበት እንዲሁም የገጠር መሬት መረጃ ሥርዓት የሚዘረጋበት ሂደት ነው፤

**WHEREAS**, it has become necessary to sustainably conserve and develop natural resources and transfer them to the coming generation through the preparation and implementation of a sustainable rural land use planning considering the different agro-ecological zones of the country;

**WHEREAS,** it has become necessary to establish an inclusive land administration and use system that ensures and strengthens the land rights of women and vulnerable groups;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (2) (a) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**<u>PART ONE</u>**

**<u>GENERAL</u>**

**1. <u>Short title</u>**

This Proclamation may be cited as "Rural Land Administration and Use Proclamation No. 1324/2024".

**2. <u>Definition</u>**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "Rural Land" means land outside of a municipality holding or a town designated as such by the relevant law;

2/ "Rural Land Information System" means a system of recording, organizing, analyzing, and updating rural land and land-related information and disseminating of same to stakeholders;

3/ "Rural Land Registration" means the process of recording and organizing land information pertaining to rural landholding and land use rights';

4/ "Rural Land Administration" means a process whereby rural land holding rights are recognized and recorded, tenure security ensured, land property valued, a land use plan is prepared and implemented, land dispute among land users is resolved, and obligations of land users enforced as well as rural land information system developed;

፭/ “የገጠር መሬት አጠቃቀም” ማለት የገጠር መሬትን በእንክብካቤ ይዞ ዘላቂነት ባለው መንገድ ለተሻለ ጠቀሜታ እንዲውል የሚደረግበት ሂደት ነው፤

፮/ “የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ” ማለት አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የገጠር መሬት ሊሰጥ ከሚችለው የተለያዩ የመሬት አጠቃቀም አማራጮች መካከል የመሬት መጎሳቆልንና የአካባቢን ብክለት ሳያስከትሉ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙት አማራጮች የሚወሰኑበትና ተግባራዊ የሚደረጉበት የአሰራር ዘዴ ነው፤

፯/ “አካባቢያዊና ተሳትፏዊ የመሬት አጠቃቀም” ማለት በገጠር ቀበሌ በማሳ ደረጃ መሠረት አድርጎ በሚዘጋጅ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅት ላይ የሚኖር ማህበረሰባዊ ተሳታፊነት ነው፤

፰/ “አርሶ አደር” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት መደበኛ ወይም ቋሚ መተዳደሪያው የእርሻ ሥራ የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፤

፱/ “አርብቶ አደር” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት መደበኛ ወይም ቋሚ መተዳደሪያው እንስሳት በማርባት ላይ የተመሰረተ ሰው ነው፤

፲/ “ከፊል አርብቶ አደር” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት መደበኛ ወይም ቋሚ መተዳደሪያው እንስሳት በማርባት እና በእርሻ ሥራ የሚተዳደር ነው፤

፲፩/ “ማሣ” ማለት በአንድ ቦታ ላይ የሚገኝ በድንበር የተወሰነና በባለይዞታው ስር ያለ መሬት ነው፤

፲፪/ “የግል ይዞታ” ማለት በአንድ ባለይዞታ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ባለይዞታዎች በጋራ ይዞታ ስር ያለ የገጠር መሬት ነው፤

፲፫/ “የወል ይዞታ” ማለት አርሶ አደሮች ወይም አርብቶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ፣ ለደንና ለማህበራዊ አገልግሎቶች የሚጠቀሙበት የጋራ የገጠር መሬት ነው፤

፲፬/ “የመንግስት ይዞታ” ማለት በወል ወይም በግል ይዞታ ያልተያዘ መሬት ሲሆን የመንግስት ተቋማት ይዞታዎችን፣ የደን መሬቶችን፣ የዱር እንስሳትና ጥብቅ ቦታዎችን፣ ሀይቆችን፣ ወንዞችንና ሌሎችን በተመሳሳይ መልኩ የተያዙትን ያጠቃልላል፤

፲፭/ “ሕገ ወጥ የመሬት ይዞታ” ማለት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የተያዘና አግባብ ባለው አካል እውቅና ያልተሰጠው ማናቸውም የገጠር መሬት ይዞታ ነው፤

5/ “Rural Land Use” means a process whereby rural land is conserved and sustainably used in a manner that gives better output;

6/ “Rural Land Use Plan” means a practice whereby the options that give better economic benefits without causing land degradation and environmental pollution are determined and implemented from among the different use options a rural land can give on the basis of physical, economic, and social information;

7/ "Local and Participatory Land Use" means community participation in the preparation of parcel based land use plan in a rural kebele;

8/ "Farmer" means any person, whose livelihood depends on farming activites as per this Proclamation;

9/ "Pastoralist" means a person, whose livelihood depends on livestock production as per this Proclamation;

10/ “Semi-pastoralist" means a person, whose livelihood depends on livestock production and farming activites as per this Proclamation;

11/ “Parcel” means a portion of land that has its own boundary for which distinct rights exist;

12/ “Private Landholding” means rural land held by an individual or jointly by more landholders;

13/ “Communal Landholding” means rural land that farmers, pastoralists, and semi-pastoralists use in common for grazing, forest, and other social services;

14/ “State Landholding” means land which is not held as communal or private and includes land holdings of government organs, forest lands, wildlife, and protected areas, lakes, rivers, and other similar holdings;

15/ "Illegal Landholding" means any rural landholding held illegally and not recognized by the appropriate body;

፲፮/ “የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት የይዞታ ባለመብት መሆኑን ለማረጋገጥ በመሬት አስተዳደር ተቋማት የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

፲፯/ “አስተዳደራዊ ውሳኔ” ማለት መሬት ለማስተዳደር ስልጣን የተሰጣቸው እና ከመሬት ይዞታና አጠቃቀም ሂደቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚያስፈፅሙ ተቋማትን የሚያመላክት ሆኖ በሕግ የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር በሚፈፅሙበት ጊዜ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ የሚሰጥ ውሳኔ ሲሆን የገጠር መሬት ምዝገባን፤ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አሰጣጥን፣ ከመሬት አጠቃቀም ዕቅድ እና ከሌሎች ተዛማጅ እርምጃዎች ጋር በተገናኘ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ያጠቃልላል፤

፲፰/ “መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት” ማለት ቢያንስ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሠረት፣ የመንግሥት አካል ያልሆነ፣ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ያልወከለ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ሕጋዊ ዓላማን ለማሳካት አግባብ ባለው ሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አካል ነው፤

፲፱/ “የሃይማኖት ተቋም” ማለት ሰዎች የመረጡትና የተቀበሉትን ሃይማኖት ይዘው በይፋ ለማምለክ ፣ ለመከተል፣ ለመተግበር ፣ ለማስተማር ፣ ለመግለፅ ወይም ለማስፋፋት እንዲያስችላቸው ያደራጁትና ዓላማው ለትርፍ ያልሆነ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤

፳/ “ማህበራዊ ተቋማት” ማለት የማህበረሰብ አባላትን ችግር ለመፍታት በማህበረሰቡ ፍቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የተቋቋሙ አደረጃጀቶች ናቸው፤

፳፩/“ክፍፍል” ማለት ያልተያዘ ወይም በተለያየ ምክንያት በዚህ ሕግና በክልል ሕጎች ከባለይዞታዎች የተነጠቀ ወይም የተለቀቀ የገጠር መሬት፤ መሬት ለሌላቸው ወይም መሬት ላነሳቸው ሰዎች መስጠት ነው፤

፳፪/“ሽግሽግ” ማለት የገጠር መሬት በፍትሃዊነት ለተጠቃሚዎች እንዲዳረስ ለማድረግ ይዞታ ካላቸው በመቀነስ ለሌላቸው ወይም ይዞታቸው አነስተኛ ለሆኑ ሰዎች የመስጠት ተግባር ነው፤

16/ "Landholding Certificate" means a document issued by land administration institutions to prove holding right;

17/ "Administrative Decision" refers to institutions that are authorized to administer land and carry out issues related to landholding right and use processes, and it is a decision that is given on administrative issues on people's rights or interests, and registration of rural land; that includes the issuance of landholding certeficate, land use planning and other related measures, when they exercise their powers and duties given by law;

18/ "Non-Governmental Organization" means a non partisan, not for profit entity established at least by two or more persons on voluntary basis and registerd by competent authority to carry out any lawfull purpose;

19/ "Religious Institution" means a non-profit organization registered by a body authorized by law to enable people to publicly worship, follow, practice, teach, express or propagate their chosen and accepted religion;

20/ "Social Institutions" means organizations established based on the will of communities to solve problems of community members;

21/ “Distribution” means the allocation of unoccupied land or land which has been reclaimed from holders because of violations of obligations prescribed in this Proclamation or other regional laws, or land that was voluntarily relinquished by previous holders to those who are landless or with small holding size;

22/ “Re-distribution” means the transfer of land from those who have excess land to those who have none or hold a small size to ensure equity in landholding;

፳፫/ "ድጋፍ የሚሹ ሰዎች" ማለት ባለባቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ምክንያት በመሬት የመጠቀም መብት ያላገኙ ወይም የመጠቀም መብት ቢኖራቸውም እንኳን መብታቸውን ተከራክረው ሊያስከብሩ የማይችሉ እንደ ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት፣ አረጋዊያንና አካል ጉዳተኞችን ያጠቃልላል፤

፳፬/ "መሬትን ለጋራ አራሽ መስጠት" ማለት አንድ ባለይዞታ ይዞታውን ሌላ ሰው በክልሎች በሚወሰን ጊዜ እንዲያለማው እና ከዚሁ የሚገኘውን ምርት በሚስማሙት መጠን መሠረት ለመካፈል የሚስማሙበት ውል ነው፤

፳፭/ "ብሔራዊ የጂኦዴቲክ መነሻ ነጥብ" ማለት በአገር አቀፍ ደረጃ ስልጣን በተሰጠው አካል የተመሠረተ የብሔራዊ የጂኦዴቲክ የምድር መቆጣጠሪያ ነጥቦች መረብ አካል የሆነና ለቀጣይ የቅየሳ ሥራ መነሻ ሆኖ የሚያገለግል ነው፤

፳፮/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፵፯ መሠረት የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፳፯/ "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤

፳፰/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፤

፳፱/ በዚህ አዋጅ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴት ፆታንም ያካትታል፡፡

**፫. የአዋጁ ተፈፃሚነት ወሰን**

፩/ ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ በማንኛውም የገጠር መሬት እና በከተማ ክልል ውስጥ ያሉ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ውስጥ የተወሰኑ የገጠር ቀበሌዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በከተማ ወሰን ውስጥ በተጠቃለሉ ነገር ግን ርክክብ ባልተደረገባቸው ይዞታዎች ላይም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የገጠር መሬት አስተዳደር

### ንዑስ ክፍል ፩

### የገጠር መሬት ስለማግኘትና ስለመጠቀም

23/ "Vulnerable Groups" means such people as orphans, people of old age, and disabled who do not have landholding rights or, even if they have one, cannot protect their rights because of their economic and social problems;

24/ "Share Cropping" means a contract where a landholder agrees, for a period of time to be determined by regions, with another person to use his landholding in exchange for a share of the crop;

25/ "National Geodetic Reference Point" means a point established by a nationally authorized organ; a part of the national geodetic control points network which serves as a starting point for future surveying activity;

26/ "Region" means any region referred to under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Dire Dawa City Administration;

27/ "Ministry" means the Ministry of Agriculture;

28/ "Person" means any natural or juridical person;

29/ In this Proclamation, any expression in the masculine gender shall include the feminine.

**3. Scope of Application**

1/ This Proclamation shall apply to any rural land in Ethiopia and certain rural kebeles in the Regions and City Administrations in urban areas.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, this Proclamation shall apply to lands that are incorporated into urban boundaries but where such lands have not yet been officially handed over to the urban administration.

## PART TWO

## RURAL LAND ADMINISTRATION

### SECTION 1

### ACCESS AND USE OF RURAL LAND

**፬. <u>የገጠር መሬት ከመንግስት ስለማግኘት</u>**

፩/ በግብርና ሥራ እየተዳደረ ያለ ወይም ለመተዳደር የሚፈልግ ሰው የገጠር መሬት በዚህ ሕግ መሠረት በነፃ የማግኘት መብት አለው፡፡

፪/ በግብርና ሥራ ለመተዳደር የገጠር መሬት እንዲሰጠው የሚጠይቅ አመልካች ዕድሜው ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሎች ለሴቶችና ወጣቶች እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች አወንታዊ ድጋፍ የሚወሰንበትን አግባብ በሕግ ይወስናሉ፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) ላይ ያሉት ድንጋጌዎች ተደራጅተው ለሚመጡ ወጣቶችም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ፲፰ አመት ያልሞላቸው ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት፣ ወላጆቻቸው በገጠር ይኖሩ የነበሩና የራሳቸው መሬት ያልነበራቸው ከሆነ የገጠር መሬት የማግኘት መብት አላቸው፡፡

፮/ በትዳር ላይ ካሉ ተጋቢዎች አንዱ የግልም ሆነ የጋራ ይዞታ ከሌለው እንደ ማንኛውም መሬት አልባ አመልካች መሬት የማግኘት መብት አለው፡፡ የሚሰጠው መሬትም የግል ይዞታው ሆኖ ይመዘገባል፡፡

፯/ የመሬት ይዞታው ሁለቱም ተጋቢዎች የግል ይዞታ ሳይኖራቸው የተገኘ ከሆነ የሁለቱም የጋራ ይዞታ ሆኖ ይመዘገባል፡፡

**፭. <u>መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራዊ ተቋማት እና የግል ባለሀብት የገጠር መሬት የማግኘት መብት</u>**

፩/ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራዊ ተቋማት ክልሎች በሚያወጧቸው ሕጎች መሠረት ለዓላማቸው ማሳኪያ የሚውል የገጠር መሬት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ለተገለፁት ተቋማት በገጠር መሬት የመጠቀም መብት በጊዜ የተገደበ ሲሆን ጊዜውም በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች ይወሰናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) የተጠቀሱት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመሬት ላይ የሚኖራቸው መብት የመጠቀም መብት ብቻ ሲሆን የማከራየት፣ ለጋራ አራሽ የመስጠት፣ የማውረስ፣ በስጦታ የማስተላለፍ፣

**4. <u>Access to Rural Land Through Government Allocation</u>**

1/ A person may have the right to freely access rural land where he has been engaged or prefer to engage in agricultural activities for a living.

2/ Applicants shall be above 18 years of age.

3/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, regional laws may create affirmative action rules for women and youths as well as persons with disablities.

4/ The provisions in Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall also apply to organized youths.

5/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, orphans who are below 18 years of age whose parents used to live in rural areas and did not have their own land holdings shall have the right to get rural land.

6/ Where one of the spouses does not have joint or private holding, he shall have the right to access land, like any landless person. The land granted shall be registered as a private holding of such a person.

7/ Where the landholding is acquired during their marriage and both spouses do not have private holding, it will be registered as common property of both spouses.

**5. <u>The Right of Non-Governmental Organizations, Social Institutions and Private Investors to Access Rural Land</u>**

1/ Non-Governmental organizations and social institutions may have the right to access rural land as per regional laws.

2/ The rural land use right of institutions mentioned under Sub-Article (1) of this Article shall be limited by time and such period shall be determined by regional laws.

3/ The land users mentioned under Sub-Article (1) and (2) of this Article shall have only use right over the land, and they may not lease, sharecrop, bequeath, donate, create partnership contracts over

ከባለሃብት ጋር በጋራ የማልማት፣ ለብድር ዋስትና የማስያዝ መብት አይኖራቸውም፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሱት ማህበራዊ ተቋማት ይዞታቸውን ከማውረስ እና በስጦታ ከማስተላለፍ ውጭ ለባለይዞታዎች የተሰጡ መብቶች ሁሉ ይኖራቸዋል፡፡

፭/ በገጠር ልማት ለሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች በፌደራልና በክልል የኢንቨስትመንት ሕጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**፮. <u>በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ</u>**

፩/ የአርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች እና የሃይማኖት ተቋማት በይዞታቸው ላይ ያላቸው መብት የጊዜ ገደብ የለውም፡፡

፪/ የሌሎች ተጠቃሚዎች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ ክልሎች በሚያወጧቸው ሕጎች መሠረት ይወሰናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) የተደነገጉት ቢኖሩም መንግስት የገጠር መሬት ለህዝብ ጥቅም ለመውሰድ ያለውን ስልጣን የሚነካ አይሆንም፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ፪</u>

## <u>የገጠር መሬት የይዞታ ዓይነቶች እና ባለይዞታዎች በመሬታቸው ላይ ስለሚኖራቸው መብት</u>

**፯. <u>የይዞታ ዓይነቶች</u>**

በገጠር መሬት ላይ ያሉ የይዞታ ዓይነቶች የግል፣ የወል እና የመንግስት ናቸው፡፡

**፰. <u>የይዞታ መብት</u>**

፩/ ለአርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች ፣ ከፊል አርብቶ አደሮች እና የሃይማኖት ተቋማት የተሰጠው በመሬት ላይ ያላቸው መብት የይዞታ መብት ነው፡፡

፪/ የገጠር መሬት የይዞታ መብት በመሬቱ መጠቀምን፣ ማከራየትን፣ ለጋራ አራሽ መስጠትን፣ የመጠቀም መብቱን በዕዳ ዋስትና ማስያዝን፣ ከባለ ሃብት ጋር በጋራ ማልማትን፣ በውርስ ወይም በስጦታ ማስተላለፍን፣ በገጠር መሬት ይዞታ ላይ የተፈራን ንብረት በሽያጭ ማስተላፍን፣ ኩታ ገጠም ማድረግን፣ ይዞታን ማቀራረብን፣ የግል ይዞታን በኩታ ገጠም (በክላስተር) ማረስን እንዲሁም በሌላ የገጠር መሬት መለወጥን ያጠቃልላል፡፡

the land with investors, or mortgage the land use right.

4/ Social institutions referred to under Sub-Article (1) of this Article shall have all holding rights other than bequeathing and gifting.

5/ Private investors who intend to engage in rural development shall have the right to access rural land as per regional investment laws and policies.

**6. <u>Duration of the Right to Use Rural Land</u>**

1/ The landholding rights of farmers, semi-pastoralists, pastoralists and Religious Institutions have no time limit.

2/ The duration of land use rights of other users shall be determined by regional laws.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the eminent domain power of the government to expropriate land may not be restricted.

## <u>SECTION TWO</u>

## <u>THE HOLDING TYPES OF RURAL LAND AND THE RIGHTS OF HOLDERS ON THEIR LAND</u>

**7. <u>Holding Types</u>**

Rural land holding types include private, communal, and state holdings.

**8. <u>Holding Right</u>**

1/ The right that farmers, pastoralists, semi-pastoralists, and Religious Institutions have over their land is a holding right.

2/ Holding right includes the rights of use; lease; sharecrop; collateralize the use right; jointly develop the land with investors; bequeath; donate; transfer through sale or in any form properties fixed on the holding; consolidate; exchange with similar rural land holding, and cultivate the land through cluster arrangement.

## ፱. ከራይ

፩/ የገጠር መሬት ባለይዞታ የመጠቀም መብቱን በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች ለሚወሰን የጊዜ ገደብ እና የመሬት መጠን ማከራየት ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኪራይ ዘመኑ ለዓመታዊ ሰብል ከ ፲ ዓመት እንዲሁም ለቋሚ ተክል ከ ፴ ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አቅመ ደካሞች፣ እማወራዎች፣ ህጻናት፣ እንዲሁም በተለያየ ምክንያት ይዞታቸውን ለማልማት ያልቻሉ ባለይዞታዎች ይዞታቸውን ሙሉበሙሉ ከማከራየት አይከለከሉም፡፡

፬/ የኪራይ ውሎች በጽሁፍ መደረግና በክልል ስልጣን በተሰጠው ተቋም መረጋገጥና መመዝገብ አለባቸው፡፡

## ፲. መሬት ማስተላለፍን የተመለከቱ መረጃዎችን ስለማደራጀትና ስለመስጠት

፩/ የክልል የገጠር መሬት አስተዳደር ተቋማት በክልል ፣ በዞን ፣ ልዩ ወረዳ ፣ ከተማ ፣ በወረዳና በቀበሌ ጽ/ቤታቸው በኩል አከራዮችና ተከራዮችን፣ ይዞታቸውን መለዋወጥ የሚፈልጉ ባለይዞታዎችን እንዲሁም ይዞታቸውን ከባለሀብት ጋር በጋራ ማልማት የሚፈልጉትን ባለይዞታዎች እየመዘገበ የሚያገናኝ እና የአካባቢውን የመሬት ገበያ እያጠና መረጃ የሚሰጥ ክፍል ያቋቁማሉ፡፡

፪/ የክፍሉ አደረጃጀትና የአሰራር ሥርዓት በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች ይወሰናል፡፡

## ፲፩. ስጦታ

፩/ የገጠር መሬት ባለይዞታ ይዞታውን በቤተሰብ ሕጉ የስጋ ዘመዳሞች መካከል በስጦታ ወይም በውልበተደገፈ በይጦረኛል ሥምምነት ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለይዞታው በውል በተደገፈ የይጦረኛል ስምምነት ውል ለገባለት ለማንኛውም ሰው በስጦታ ማስተላለፍ ይችላል፡፡

## 9. Lease

1/ A rural landholder may lease out part or all of his land holding for a specific period of time that shall be determined by regional laws.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the lease period may not be more than 10 years for annual crops and 30 years for perennial crops.

3/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the elderly, female-headed households, children, and other people who cannot cultivate their land for valid reasons may not be restricted from leasing out the whole of their landholding.

4/ Lease contracts shall be authenticated and registered before an institution authorized by regional governments.

## 10. Organizing And Providing Information Related to Land Transfers

1/ Regional Rural Land Administration Institutions shall establish working teams in their Regional, Zone, Special Woreda, City, Woreda, and Kebele offices that may gather and provide information about potential lessors and lessees, landholders who intend to exchange their holdings as well as jointly develop their holdings with investors. Such working teams shall conduct assessments on the local land market, and avail information to interested parties.

2/ The Organization and workflow of the team shall be determined by regional laws.

## 11. Donation

1/ A landholder may donate his landholding to his relatives by consanguinity as provided in the Family Code or through maintenance contractual agreement.

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the landholder may transfer his holding through gift to any person through maintenance contractual agreement.

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) በተደነነገገው መሠረት ስጦታ ሲደረግ አካል ጉዳተኞችን እና ዕድሜያቸው ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን የሚጎዳ ከሆነ በሕግ ፊት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ የስጦታ ውል የይፍረስልኝ ወይም ክስ በውሉ ላይ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ ከተጣሰበት ወይም መጣሱን ስጦታ ሰጪው ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ ፪ ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

፭/ ማንኛውም የስጦታ ውል በጽሁፍ ሆኖ በክልል ስልጣን በተሰጠው ተቋም ቀርቦ መረጋገጥና መመዝገብ አለበት፡፡

## ፲፪. <u>ውርስ</u>

፩/ የገጠር መሬት ባለይዞታ ይዞታውን በፍትሐ ብሔር ሕጉ የውርስ ድንጋጌዎች መሠረት ለማንኛውም ሰው ማውረስ ይችላል፡፡

፪/ ባለይዞታው በኑዛዜ ሳያወርስ በሞተ ጊዜ ወይም ኑዛዜው ፈራሽ ከሆነ የፍትሐ ብሔር ሕጉ ያለ ኑዛዜ የውርስ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ፲፫. <u>መሬትን ለጋራ አራሽ መስጠት</u>

፩/ የገጠር መሬት ባለይዞታ ይዞታውን በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች ለሚወሰን የጊዜ ገደብ እና የመሬት መጠን ለጋራ አራሽ ለመስጠት ይችላል፡፡

፪/ የጋራ እርሻ ውል በጽሁፍ መደረግና በክልል ስልጣን በተሰጠው ተቋም ቀርበው መረጋገጥና መመዝገብ አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይዞታቸውን ለማልማት የማይችሉ ሰዎች እንደ አቅመ ደካሞች፣ እማወራዎች፣ ህጻናት፣ በተለያየ ምክንያት ይዞታቸውን ለማልማት ያልቻሉ ሰዎች ይዞታቸውን ሙሉ በሙሉ ለጋራ እርሻ ከመስጠት አይከለከሉም፡፡

፬/ ተዋዋይ ወገኖች ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች እና በተዋዋይ ወገኖች ውል ይወሰናል፡፡

3/ Where gifting contract is made in accordance with the provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the contract shall not apply in case it is prejudicial to minor children and persons with disabilities

4/ An application for cancellation of the conditional contract referred to in Sub-Article (1) of this Article shall be made within two years from the time the donor becomes aware of the non-performance of the contract.

5/ A contract of donation shall be made in writing and be authenticated and registered before an institution authorized by Regional Governments.

## 12. <u>Inheritance</u>

1/ A landholder may bequeath his holding to any person in accordance with the Succession Provisions of the Civil Code.

2/ Where the landholder dies intestate, or where the will is invalidated, the Succession Provisions of the Civil Code shall apply.

## 13. <u>Sharecropping</u>

1/ A landholder may sharecrop part or all of his land holding for a specific period of time that shall be determined by Regional Laws

2/ A sharecropping contract shall be made in writing and be authenticated and registered before an institution authorizd by Regional Governments.

3/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the elderly, female-headed households, children, and other people who cannot cultivate their land for valid reasons may not be restricted from sharecropping the whole of their landholding.

4/ The rights and obligations of the parties in a sharecropping contract shall be determined by the contracting parties and by the laws to be enacted by Regions.

## ፲፬. ይዞታን ከባለሀብት ጋር በጋራ ስለማልማት

፩/ የገጠር መሬትን በጋራ ለማልማት የመሬት ባለይዞታው በመሬቱ የመጠቀም መብቱን እንደ ካፒታል መዋጮ በማድረግ ከባለሀብት ጋር በሚገባው ውል መሠረት የልማት ሥራ ሊሰራ ይችላል፡፡

፪/ ይዞታን ከባለሀብት ጋር በጋራ የማልማት ውል በጽሁፍ መደረግና በክልል ስልጣን በተሰጠው ተቋም ቀርቦ መረጋገጥና መመዝገብ አለበት፡፡

## ፲፭. በይዞታ የመጠቀም መብትን ለብድር ዋስትና ስለማስያዝ

፩/ የገጠር መሬት ባለይዞታ የመጠቀም መብቱን በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች ለሚወሰን የጊዜ ገደብ ለፋይናንስ ተቋማት ለብድር ዋስትና ማስያዝ ይችላል፡፡

፪/ የገጠር መሬት የመጠቀም መብትን በመጠቀም አበዳሪዎች የሚሰጡት የብድር መጠን የተበዳሪውን ዕቅዶች ሊያሳካ የሚችል እንዲሆን የመሬቱን እምቅ አቅም ከፍተኛ ጣሪያ መሠረት ማድረግ አለባቸው፡፡

፫/ የገጠር መሬት ባለይዞታ የመጠቀም መብቱን ሌላ ሰው ከፋይናንስ ተቋማት ለሚበደረው ብድር ዋስትና ማስያዝ ይችላል፡፡

፬/ አበዳሪና ተበዳሪ የብድር መመለሻ ጊዜንና ብድሩ በሙሉ ወይም በከፊል ባይመለስ አበዳሪ መሬቱን ሊይዝ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ በግልፅ በውላቸው ላይ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

፭/ ብድሩ ባለመመለሱ ምክንያት የአበዳሪው በዋስትና የያዘውን መሬት የመጠቀም መብት ከ ፲ ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡

፮/ ተበዳሪ በውላቸው በተጠቀሰው ጊዜ ብድሩን ያልከፈለ ከሆነ አበዳሪ በውሉ ለተጠቀሰው ጊዜ ያህል ብቻ በመሬቱ የመጠቀም፣ የማከራየት ወይም ለጋራ አራሽ የመስጠት መብት አለው፡፡

፯/ አበዳሪ ዕዳው ባለመከፈሉ በውሉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ በዋስትና የያዘውን መሬት በመጠቀም ከአበደረው ገንዘብ የበለጠ ጥቅም ቢያገኝ ተበዳሪ ከዚህ የመጠየቅ መብት የለውም፡፡

፰/ ብድሩ በከፊል ባልተከፈለ ጊዜ የአበዳሪው በመሬቱ ላይ ያለው የመጠቀም መብትና የአከፋፈል ሁኔታ ያልተከፈለውን ብድር ታሳቢ ማድረግ አለበት፡፡

## 14. Joint Development

1/ A landholder may enter into a joint development contract with an investor by contributing his use right as a capital contribution.

2/ A joint development contract shall be made in writing and be authenticated and registered before an institution authorized by Regional Governments.

## 15. Using Land Use Rights as Collateral

1/ A landholder may collateralize his use right to financial institutions for a period of time that shall be specified under regional laws.

2/ Financial institutions shall consider the maximum potential of the land when providing credit to the landholder.

3/ A landholder may collateralize his use right as suretyship.

4/ Contracting parties shall stipulate under their contract the time for the repayment of the debt, and the length of time that the creditor may use the land where the debtor fails to pay the whole or part of the debt.

5/ The land use right of the creditor over the collateralized land shall not exceed above ten years.

6/ Where the debtor fails to pay the debt at the time prescribed in the contract, the creditor may have the right to use, lease, or sharecrop the land for the prescribed time only.

7/ Where the creditor, by using the land, generates more money than he had lent, the debtor may not claim the difference.

8/ Where the debt is partially paid, the right of the creditor to use the land shall be adjusted in accordance with the unpaid debt.

፱/ አበዳሪ ዕዳው ባለመከፈሉ በዋስትና የያዘውን መሬት በመጠቀም ከአበደረው ገንዘብ ያነሰ ጥቅም ቢያገኝ መሬቱን በውሉ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ ለመያዝ ወይም የተበዳሪውን ሌላ ንብረት በመያዝ ለዕዳው ማስፈፀሚያ ለማዋል አይችልም፡፡

፲/ ማንኛውም የማስያዣ ውል በጽሁፍ መደረግና በክልል ስልጣን በተሰጠው የወረዳ፣ ልዩወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ተቋም ቀርቦ መረጋገጥ እና መመዝገብ አለበት፡፡

፲፩/ ከላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አበዳሪና ተበዳሪ ስለሚኖራቸው ዝርዝር መብትና ግዴታ በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች ይወሰናል፡፡

፲፪/ በአበዳሪና በተበዳሪ መካከል የዋስትና የመሬት የመጠቀም መብትን በሚመለከት ለሚነሳ ማናቸውም ክርክር በእርቅ ወይም ሥልጣን ባለው መደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ መወሰን አለበት፡፡

## ፲፮. ይዞታን ስለመለዋወጥ

፩/ የገጠር መሬት ባለይዞታ ይዞታውን ከሌላ ባለይዞታ መሬት ጋር መለዋወጥ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ላይ ያለው መብት በአስተዳደር ወሰን የተገደበ አይደለም፡፡

፫/ የይዞታ ልውውጥ ውል በጽሁፍ መደረግና በክልል ስልጣን በተሰጠው ተቋም ቀርቦ መረጋገጥና መመዝገብ አለበት፡፡

፬/ ልውውጡ የሚደረገው በተለያዩ ክልሎች መካከል ከሆነ ውሉ በጽሁፍ መደረግና በፌደራል ሥልጣን በተሰጠው ተቋም ቀርቦ መረጋገጥና መመዝገብ አለበት፡፡

## ፲፯. በገጠር መሬት ይዞታ ላይ የተፈራን ንብረት በሽያጭ ስለማስተላፍ

፩/ ባለይዞታዎች በመሬት ይዞታቸው ላይ በጉልበታቸው፣ በእውቀታቸው ወይም በመፍጠር ችሎታቸው ያፈሯቸውን የማይንቀሳቀሱ ቋሚ ንብረቶች ባሉበት ሁኔታ የመሸጥ፣ የመለወጥ ወይም በሌላ በማንኛውም ሕጋዊ መንገድ የማስተላፍ መብት አላቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽፅ (፩) የተደነገጉት የማይንቀሳቀሱ ቋሚ ንብረቶች ግንባታዎችን ወይም በመሬት ላይ ሙሉ በሙሉ የለሙ ቋሚ ተክሎችን የሚያጠቃልል ሲሆን ዝርዝር መስፈርቱ በክልሎች ይወጣል፡፡

9/ The liability of the debtor shall be limited to the use right of the land transferred for the agreed time.

10/ Collateral contracts shall be made in writing and be authenticated and registered before Woreda, Special Woreda and City-Adminstration institutions authorized by regional governments.

11/ Without prejudice to the above Sub-Articles of this Article, the rights and obligations of the creditor and debtor shall be determined by regional laws.

12/ Any dispute regarding the collateral contract shall be resolved through conciliation/mediation or regular court having jurisdiction.

## 16. Exchange of Holdings

1/ A landholder may exchange his holding with another land.

2/ The right in Sub-Article (1) of this Article shall not be limited by administrative boundary.

3/ Every landholding exchange contract shall be made in writing and be authenticated and registered before an institution authorized by regional governments.

4/ Where the exchange takes place between different regions, the contract shall be made in written form, and verified and registered by authorized federal institution .

## 17. Sale of Properties Found on Landholding

1/ A landholder may sell or transfer in any other means his immovable properties fixed on the land without separating them from the land.

2/ Immovable properties referred to under Sub-Article (1) of this Article may include buildings, trees, perennial crops, and other fixtures. the detailed criteria shall be issued by Regions.

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው መብት ተፈፃሚ ሲሆን አብሮ የሚተላለፈው መሬት በክልሎች በሚወጣው ዝርዝር ሕግ እና መስፈርት መሠረት ባለይዞታውን ከይዞታው በማያፈናቅል መልኩ በመሬቱ ላይ የተፈራውን ንብረት ለመጠቀም የሚያገለግል የመሬት ስፋት ብቻ መሆን አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው መብት ተፈፃሚ የሚሆነው የመሬት አጠቃቀም ዕቅድን መሠረት በማድረግ ብቻ ይሆናል፡፡

፭/ ይህ ድንጋጌ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ሽያጭ የተመለከቱ ሌሎች ሕጎችን የሚያስቀር አይሆንም፡፡

## ፲፰.ይዞታን ኩታ ገጠም ስለማድረግ እና ስለማቀራረብ

፩/ አነስተኛ ማሳዎች ለልማት አመቺ እንዲሆኑ ባለይዞታዎች ይዞታቸውን ኩታ ገጠም ለማድረግ እና ለማቀራረብ የሚያስችል ልውውጥ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

፪/ ይዞታን ኩታ ገጠም የማድረግ እና የማቀራረብ ውል በጽሁፍ መደረግና በክልል ስልጣን በተሰጠው ተቋም ቀርቦ መረጋገጥና መመዝገብ አለበት፡፡

፫/ ይዞታቸውን ኩታ ገጠም ለማድረግ እና ለማቀራረብ ልውውጥ ለሚያደርጉ ባለይዞታዎች የሚሰጡ ማበረታቻዎችን በተመለከተ በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች ይወሰናሉ፡፡

## ፲፱. የግል ይዞታን በኩታ ገጠም ማረስ

፩/ ባለይዞታዎች ይዞታቸውን ኩታ ገጠም ባያደርጉም በኩታ ገጠም እንዲያርሱ ይበረታታሉ።

፪/ ክልሎች ይዞታቸውን በኩታ ገጠም ለሚያርሱ ባለይዞታዎች የተለያዩ ማበረታቻዎችን ማቅረብ አለባቸው፡፡

፫/ ክልሎች ይዞታቸውን በኩታ ገጠም ለሚያርሱ ባለይዞታዎች ለምርቶቻቸው የገበያ ትስስር መፍጠር አለባቸው፡፡

## ፳. ይዞታን ኩታ ገጠም ማድረግ እንዲሁም በኩታ ገጠም ማረስ አስገዳጅነት

በመንግስት ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ፕሮጀክቶች በተገነቡ የመስኖ አውታሮች ተጠቃሚ የሆኑ የመሬት ባለይዞታዎች ይዞታቸውን ኩታገጠም ማድረግ እና በኩታ ገጠም ማረስ አለባቸው፡፡

3/ Where the right stipulated in Sub-Article (1) of this Article is applied, the land to be transferred shall only be confined to the area ofland, the property to be transferred is situated in a manner that does not displace the holder; the detailed laws and criteria shall be dettremined by regions.

4/ The application of the right referred to under Sub-Article (1) of this Article shall be based on the land use plan.

5/ Relevant laws in the transfer of immovable properties shall apply in such cases.

## 18. Consolidation of Holdings

1/ Landholders may exchange their landholdings where the transaction has the effect of consolidating the holdings.

2/ Land consolidation contracts shall be made in writing and be authenticated and registered before an institution authorized by regional governments.

3/ Regional laws may provide incentives to landholders who exchange their holdings with the effect of consolidation.

## 19. Clustering

1/ Landholders may cultivate their holdings through cluster.

2/ Regional laws shall provide incentives to landholders who are cultivating their land through cluster.

3/ Regions shall create market linkage to landholders who are cultivating their land through cluster.

## 20. Mandatory Consolidation and Clustering

Landholders whose holdings are within government or non-governmental organizations' irrigation projects shall be bound by consolidation and clustering schemes laid by the government.

**፳፩. የጋራ ባለይዞታዎች ፈቃድ አስፈላጊ ስለመሆኑ**

ይህ አዋጅ በሚፈቅደው መሠረት የገጠር መሬት ይዞታ ሲተላለፍ ይዞታው የባልና የሚስት ወይም የሌሎች ባለይዞታዎች የጋራ ከሆነ መተላለፉ በሁሉም ባለይዞታዎች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡

**21. Securing the Consent of Joint Holders**

Joint holders or spouses shall consent to any landholding transfers provided in this proclamation.

## ንዑስ ክፍል ፫

## የገጠር መሬትን ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

## SECTION THREE

## RURAL LAND SURVEYING, REGISTRATION, AND CERTIFICATION

**፳፪. ይዞታን ስለመለካትና ስለማስመዝገብ**

፩/ የግል፣ የወል እና የመንግስት ይዞታዎች በዘመናዊ የቅየሳ መሳሪያዎች እየተለኩ ይመዘገባሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የተለኩት መሬቶች ባለይዞታዎች የይዞታቸውን ድንበር እና መጠን የሚያሳይ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማግኘት መብት አላቸው፡፡

፫/ መሬቱ የባልና ሚስት የጋራ ይዞታ ወይም በሌሎች ሰዎች በጋራ የተያዘ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ በሁሉም የጋራ ባለይዞታዎች ስም መዘጋጀት አለበት፡፡

**22. Surveying and Registration of Land Holdings**

1/ Private, communal, and state holdings shall be surveyed using modern surveying instruments and registered.

2/ Holders of lands surveyed and registered under Sub-Article (1) of this Article shall have the right to get a holding certificate for their parcels showing boundaries and land size.

3/ The holding certificate shall be prepared in the name of all joint holders where the land belongs to spouses or other joint holders.

**፳፫. ከአንድ በላይ ሚስት በሚኖር ጊዜ የገጠር መሬት ይዞታ ምዝገባ**

፩/ በወንጀል እና በቤተሰብ ሕጉ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባትን በሚመለከት ያለው ክልከላ እንደተጠበቀ ሆኖ በባህል ወይም በሃይማኖት ምክንያት ከአንድ በላይ ሚስቶች በሚኖሩበት ጊዜ በመሬቱ ለመጠቀም ሲባል የሴቶችን መብት በሚያስጠብቅ ሁኔታ ምዝገባ መደረግ አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ሕግ መውጣት በኋላ ባል ከአንድ በላይ ጋብቻ የሚመሠርት ከሆነ ከመጀመሪያ ሚስቱ ጋር ያለው ጋብቻ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቀድሞ ሚስቱ ጋር ያላቸውን የመሬት ይዞታ ክፍፍል በማድረግ የመሬቱ መረጃ በየድርሻቸው ወቅታዊ መደረግ አለበት፤ እንዲሁም አዲስ ከመሠረተው የትዳር አጋሩ ጋር የሴቶቹን መብት በሚያስጠብቅ ሁኔታ በራሱ ድርሻ ዳግም የይዞታ ምዝገባ ማድረግ አለበት

**23. Registration of Rural Landholdings of Couples in a Polygamous Marriage**

1/ Without prejudice to the prohibition of polygamy under the Criminal and Family Codes, where a person has two or more wives the landholding shall be registered in a manner that protects the rights of all the wives in the polygamous marriage.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article where a husband concludes polygamous marriage after entering into force of this Proclamation, the common land property of the husband and the first wife shall be partitioned, updated, and registered in the name of each spouse. The share of the husband shall be re-registered with his new spouse in a manner that protects the rights of the women.

**፳፬. ስለ የወል መሬት ይዞታ አስተዳደርና ምዝገባ**

፩/ ክልሎች የወል መሬትን የሚያስጠብቁ የአስተዳደርና አያያዝ ሕጎችን ያወጣሉ፡፡

**24. Communal Landholding Administration and Certification**

1/ Regions may issue land administration and management laws that protect and conserve communal lands.

፪/ የወል መሬት ተጠቃሚዎች የሕግ ሰውነት የሚኖራቸው ሲሆን የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

፫/ የወል መሬት ባለይዞታዎች የወል የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተጠቃሚው ህብረተሰብ ስም ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል፡፡

## ንዑስ ክፍል ፬

## ሽግሽግና ክፍፍል

**፳፭. ሽግሽግ**

፩/ የግል እና የወል የመሬት ይዞታዎች በሽግሽግ አይከፋፈሉም፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በመንግስት ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ በተገነቡ የመስኖ ፕሮጀክቶች ውስጥ ያሉ ይዞታዎች ላይ ሽግሽግ ሊካሄድ ይችላል፡፡

፫/ የመስኖ መሬት ሽግሽግ በሚደረግበት ጊዜ የሴቶችና ድጋፍ የሚሹ ሰዎችን በመሬት የመጠቀም መብትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

፬/ በመስኖ መሬት ላይ ስለሚደረግ ሽግሽግ ዝርዝሩ በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች ይወሰናል፡፡

**፳፮. ክፍፍል**

፩/ የመሬት ክፍፍል፡-

ሀ) የመሬት ባለይዞታዎች በህይወት የሌሉና ወራሽ የሌላቸው ከሆኑ፣

ለ) ባለይዞታዎቹ በሰፈራ ወይም በፍላጎታቸው በክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ ከሚወሰነው ሁኔታና የጊዜ ገደብ በላይ ከአካባቢው ለቀው የቆዩ ከሆነ፣

በአካባቢው ለሚኖሩ የገጠር መሬት ለሌላቸው ወይም መሬት ላነሳቸው አርሶ አደሮች በክፍፍል ይሰጣሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት አካባቢውን ለቀው የሄዱ ሰዎች ይዞታ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

2/ Users of communal land shall have legal personality and working procedure shall be established.

3/ A communal landholding certificate shall be issued in the name of the user community.

## SECTION FOUR

## REDISTRIBUTION AND DISTRIBUTION

**25. Re-distribution**

1/ Private and communal holdings may not be re-distributed.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, landholdings within government and non-governmental organization funded irrigation structures may be re-distributed.

3/ Irrigation land re-distribution shall consider the land rights of women and vulnerable groups.

4/ The details of irrigated land re-distribution shall be determined by regional laws.

**26. Distribution**

1/ Distribution of land:

The land holding shall be distributed to those who do not have rural land or to those who have small size land holding. Where:

a) A land holder is deceased and has no heirs;

b) A land holder has left his area of residence due to settlement or their desire for more than the time limit and conditions determined by the rural land administration laws of the regions.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the landholdings of landholders who left their locality due to natural or man-made disasters may not be distributed.

፫/ ሊለሙ የሚችሉ ተራራማና በረቦራማ የሆኑ መሬቶችን በጥናት ላይ በመመስረት በመሬቱ ላይ ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ በክፍፍል ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፭ (፩) እና በዚህ አንቀፅ መሠረት መሬት ሲሰጥ የመሬት አጠቃቀም ዕቅዱን ወይም ጥናቱን መሠረት ተደርጎ መሆን አለበት፡፡

፭/ ክፍፍል በሚደረግበት ጊዜ የገጠር መሬት የሌላቸው እንደ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት፣ አቅመ ደካሞች ላሉ በየክልሉ የሚወጡ ሕጎች ቅድሚያ ሊሰጡ ይገባል፡፡ ይህም ሲደረግ የገቢ መጠንን፣ የቤተሰብ ብዛትንና የመሳሰሉትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ቅደም ተከተል በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች ሊደነግጉ ይገባል፡፡

**፳፯. <u>ዝቅተኛ የማሳ እና ከፍተኛ የይዞታ መጠንን ስለመወሰን</u>**

፩/ አንድ ባለይዞታ ሊኖረው የሚገባው ዝቅተኛ የማሳ እንዲሁም ከፍተኛ የገጠር መሬት ይዞታ መጠን ክልሎች በሚያወጡት ሕግ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

፪/ የገጠር መሬት ይዞታ በማንኛውም መንገድ በሚከፋፈልበት ወቅት የሚከፋፈለው የመሬት ይዞታ መጠን ከዝቅተኛው የማሳ መጠን በታች መሆን የለበትም፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (፪) የተደነገገው ባልና ሚስት ፍቺ በሚፈፅሙበት ጊዜ የሚያደርጉትን የመሬት ይዞታ ክፍፍል አይመለከትም፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ፭</u>

## <u>የመሬት አጠቃቀምና ልማት ዕቅድ</u>

**፳፰. <u>መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ስለማዘጋጀት</u>**

፩/ የፌደራል መንግስት መሬትን በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል የመሬቱን ተስማሚነት መሠረት ያደረገ አገር አቀፍ መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡

፪/ ክልሎች የአገር አቀፉን መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት በማድረግ የክልል መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ያዘጋጃሉ፡፡

፫/ በተዋረድም የክልሉን መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት በማድረግ ዝርዝር የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መዘጋጀት አለበት፡፡

3/ Cultivable mountainous and gully lands may be distributed to the landless based on studies and in a manner that may not cause damage to the land.

4/ where land is allocated according to Article 5(1) of this Proclamation and this Article, it shall be based on the land use plan or study.

5/ Regional laws shall give priority to landless women, youth, orphans, and people with disabilities in distribution programs. Regional laws shall consider, *inter alia*, the income and family size of applicants to access lands to be distributed.

**27. <u>Minimum Parcel and Maximum Holding Size</u>**

1/ Minimum parcel and maximum holding size shall be determined by regional laws.

2/ When the rural holding is distributed in any manner, the land to be distributed should not be below the minimum parcel size.

3/ Sub-Article (2) of this Article may not apply to the partition of matrimonial landholdings following the dissolution of marriage.

## <u>SECTION FIVE</u>

## <u>LAND USE AND DEVELOPMENT PLAN</u>

**28. <u>Preparing Master Land Use Plan</u>**

1/ The Federal Government shall prepare a national master land use plan based on the suitability of the land and which ensures sustainable land utilization.

2/ Regions shall prepare a regional master land use plan based on the national master land use plan.

3/ A detailed land use plan shall be prepared based on the regional master land use plan.

**፳፱. አካባቢያዊ ተሳትፏዊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ስለማዘጋጀት**

በሚዘጋጀው ማንዋል መስፈርት መሠረት አካባቢያዊ ተሳትፏዊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መዘጋጀት አለበት፡፡

**፴. መሬት አጠቃቀም ዕቅድን ወቅታዊ ስለማድረግ**

፩/ የአገር አቀፍና የክልል መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅዶች እንዲሁም የአካባቢያዊ ተሳትፏዊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በዕቅድ ሰነዱ በሚወሰን የጊዜ ገደብ መከለስ ወይም ወቅታዊ መደረግ አለባቸው፡፡

፪/ ማንኛውም የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በማንኛውም ሁኔታ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ ቅርሶች እና ቦታዎች ባሉበት ሁኔታ በአግባቡ ተጠብቀው እንዲቆዩ ማድረግ አለበት፡፡

**፴፩.የገጠር መሬት ተጠቃሚ ግዴታዎች እና መብቱን የሚያሳጡ ሁኔታዎች**

፩/ የገጠር መሬት ተጠቃሚ መሬቱን በሚወጣ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት በአግባቡ የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ባልወጣባቸው አካባቢዎች ዕቅዱ እስከሚዘጋጅ ድረስ መሬቱን በአግባቡ የመንከባከብ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ የገጠር መሬት ተጠቃሚ በመሬቱ ላይ ጉዳት ካደረሰ እንደ ጉዳቱ ክብደት የመጠቀም መብቱን እስከማጣት የሚደርስ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሠረት የገጠር መሬት ተጠቃሚ ስለሚጣልበት ግዴታ፣ መሬት ላይ ስለሚደርስ ጉዳት ዝርዝር፣ ስለሚወሰደው እርምጃ፣ የይዞታና የመጠቀም መብት ሊታጣባቸው የሚችሉ ሌሎች ዝርዝር ምክንያቶች በየክልሉ በሚወጡ ሕጎችይወሰናል፡፡

**፴፪. በገጠር መሬት አጠቃቀም ረገድ ስለተጣሉ ገደቦች**

በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፰ እና ፳፱ በተደነገገው የመሬት አጠቃቀም እና አያያዝ ሥርዓት መሠረት በሚዘጋጀው የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሚወሰን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩/ ተዳፋትነታቸው ፴ በመቶና በታች የሆኑ የገጠር መሬቶች የተጠቃሚዎች የመሬት አያያዝ የአፈር ክለትን የሚቀንስ መሆን ያለበት ሲሆን በእርጥበት አጠር አካባቢዎች ውኃን የመያዝ ስልትን ጭምር የተከተለ መሆን አለበት፤

**29. Participatory Local Level Land Use Plan**

A participatory local-level land use plan shall be prepared in accordance with the scale set in the manual to be prepared.

**30. Updating Land Use Plan**

1/ The national and regional master land use plans as well as local participatory local level land use plans shall be revised or updated on a timely basis set in the plan document.

2/ Any land use plan shall, at any time, protect and preserve religious and cultural heritages and places.

**31. Obligations of Rural Land Users and Conditions that Deprive Rights**

1/ A rural land user shall properly use the land in accordance with the land use plan issued. In areas where the land use plan is not yet issued, the land user shall properly conserve the land.

2/ Based on the gravity of the damage, measures, to the extent depriving the landholding right, shall be taken where the landholders fails to properly conserve his land.

3/ As per Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the obligations to be imposed on users of rural land, the details of the damage to the land, the measures to be taken, and the detail reasons that may result in the loss of holding and use rights shall be determined by regional laws.

**32. Restrictions Imposed on Rural Land Use**

The following restrictions shall be observed until such time that land use plans are prepared pursuant to Articles 28 and 29 of this Proclamation:

1/ The management of rural lands the slope of which is less than 30 percent shall reduce soil degradation, and in dry-land areas, a strategy of water harvesting shall also be followed;

፪/ ተዳፋትነታቸው ከ ፴፩ እስከ ፷ በመቶ የሆኑ የገጠር መሬቶችን ተጠቃሚዎች ለዓመታዊ ሰብሎች ልማት ማዋል የሚችሉት አግባብነት ያላቸውን የአፈርና ውሃ እቀባ ቴክኖሎጂዎች በመስራት ብቻ ይሆናል፤

፫/ ተጠቃሚዎች ተዳፋትነታቸው ከ ፷ በመቶ በላይ የሆኑ የገጠር መሬቶችን ከዓመታዊ ሰብልና ከልቅ ግጦሽ አገልግሎት ውጪ በማድረግ ለዛፍ፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለንብ ማነብ፣ ለእንስሳት መኖ ልማትና እንደ ሁኔታው ለቱሪስት መስህብነት ማዋል ይኖርባቸዋል፤

፬/ የመሬት ተጠቃሚዎች በማንኛውም ተዳፋት የሚገኝና በጣም የተጎዳ የገጠር መሬትን ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነፃ በማድረግ እንዲያገግምና ማገገሙ ሲረጋገጥ በሚወጣለት የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት ጥቅም እንዲሰጥ ማድረግ ይኖርባቸዋል፤

፭/ ቦረቦራማና የተጎዱ የገጠር መሬቶችን የአካባቢው ማህበረሰብ በጋራ ትብብር እንደ ፊዚካላዊና ሥነ-ህይወታዊ ሥራዎችን በመስራት እንዲያገግሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይኖርበታል፤

፮/ በኮረብታማ አካባቢዎች በቦረቦር የተጎዱ የገጠር መሬቶች በወል ወይም እንደሁኔታው በግል ይዞታ ሥር ሆነው እንዲያገግሙና መልሰው እንዲለሙ መደረግ አለባቸው፤

፯/ ማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ በቂ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሲያገኝ የተሻሻሉ ባህላዊና ሳይንሳዊ የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ዘዴዎችን የመጠቀምና የእርሻ፣ የግጦሽ እና የደን መሬቶችን ምርታማነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤

፰/ የውሃ አዘል የገጠር መሬቶች በአካባቢው ማህበረሰብና በሚመለከተው አካል በሚደረግ የሙያ ድጋፍ ተከልለው መጠበቅ እና በአግባቡ ለጥቅም መዋል አለባቸው፤

፱/ የውሃ ዳርቻዎች በጥናት ላይ ተመስርተው በተወሰነ ርቀት ተከልለው ከመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ መፈፀም አለበት፤

፲/ የሚመለከታቸው አካላት በገጠር መሬት ላይ አዳዲስ የእርሻ ኢንቨስትመንቶች ሲያቋቁሙና ሲያስፋፉ፣ የመሰረተ ልማት አውታሮች ሲዘረጉና የሰፈራ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ሲያደርጉ የአካባቢ ደህንነትን፣ ሊከሰቱ ለሚችሉ ችግሮች የመግቻ ስልቶችንና ተግባራትን በዕቅዶቻቸው አካተው መተግበር አለባቸው፤

2/ Users of rural lands, the slopes of which are between 31-60 percent, may use the land for annual crops, only after proper conservation technologies are in place;

3/ Users of rural lands, the slope of which is more than 60 percent, shall use the land for tree planting, perennial crops, bee harvesting, forage production, and tourist attraction, instead of farming and free grazing;

4/ Users must ensure that rural land of every slope which is highly degraded shall be restricted from human and animal interference for a given period of time to let it recover, and shall be put to use when ascertained that it has recovered;

5/ The local community, through joint effort, shall rehabilitate and make use of the land which is damaged and full of gullies by using biological and physical works;

6/ Rural lands in hilly areas that are damaged by gullies shall be rehabilitated and developed by putting them either under the custody of communal or private holding as the case may be;

7/ Every rural land user shall use improved traditional and scientific land use and management methods and ensure the productivity of agricultural, grazing and forest lands, after getting an adequate extension package;

8/ Wetlands shall be preserved and put to proper use by the local community and the help of the experts of relevant organs;

9/ Water banks shall be protected with in certain distance based on study and land use plan;

10/ Relevant organs shall include in their plan strategies and actions to protect environmental damages when they establish and expand new agricultural investments, construct infrastructure, and implement resettlement programs on rural lands;

፲፩/ በመስኖ መሬቶች ላይ የከተማ፣ የመንደር ምስረታና የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ግንባታ እንዲሁም ከመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ከተቀመጡ ግልጋሎቶች ውጪ መጠቀም የተከለከለ ነው፤

፲፪/ በማንኛውም የተዳፋትነት ደረጃ ያለ የገጠር መሬትን በክልሎች ሕግ መሠረት ለደን ልማት ማዋል ይቻላል፡፡

፴፫. **የልማት ዕቅድ ስለማዘጋጀት**

የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ሲዘጋጅ የልማት ዕቅዱም መዘጋጀት አለበት፡፡

፴፬. **የገጠር ቀበሌ ማዕከል ምስረታ**

የገጠር ቀበሌ ማዕከል ምስረታ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድን መሠረት በማድረግ ይቋቋማል፡፡

## ንዑስ ክፍል ፮

## የአርብቶ አደር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

፴፭. **የወል መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ስለማውጣት**

አርብቶ አደር ያላቸው ክልሎች የአርብቶ አደር የወል መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ያወጣሉ፡፡

፴፮. **የወል ይዞታ የማይከፋፈል ስለመሆኑ**

በአርብቶ አደር ማህበረሰብ ፍላጎትና የጋራ ውሳኔ እና በጥናት ተደግፎ ካልሆነ በስተቀር የወል መሬቶች በክፍፍልም ሆነ በማንኛውም መንገድ ወደ ግል ይዞታነት አይለወጡም፡፡

፴፯. **ለባህላዊ የመሬት አያያዝ ሥርዓቶች እውቅና ስለመስጠት**

፩/ በየክልሉ የሚወጡ ሕጎች ለባህላዊ ተቋማት፣ ለባህላዊ መሬት አጠቃቀምና አያያዝ እንዲሁም ለግጭት አፈታት ሥርዓት እውቅና በመስጠት ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፡፡

፪/ ባህላዊ የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ሕጎችና የግጭት አፈታት ሥርዓቶች መሠረታዊ የሆኑ ሕገ-መንግስታዊ መብቶችን፣ የሴቶችን መብት እንዲሁም በሌሎች ሕጎች የተሰጡ መብትና ግዴታዎችን የሚፃረሩ ከሆነ ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

፴፰. **የወል ይዞታን ስለማከራየት**

፩/ አርብቶ አደሮች ከወል ይዞታቸው ላይ በተጠቃሚዎች የጋራ ውሳኔ በኪራይ

11/ Development of urban and village centers, service rendering institutions as well as other services contrary to the land use plan, on irrigable lands is prohibited;

12/ Sloppy lands of any degree may be used for forest development based on regional laws.

33. **Preparing Development Plan**

A development plan shall be prepared together with the land use plan.

34. **Establishing Kebele Centres**

Rural kebele centers shall be established based on land use plans.

## SECTION SIX

## PASTORAL LAND ADMINISTRATION AND USE

35. **Issuance of Communal Land Administration and Use Law**

Regional States with pastoral population shall issue pastoral communal land administration and use laws.

36. **Prohibition of Privatization of Communal Lands**

Communal lands may not be partitioned and privatized either through distribution or any other means unless it is based on the decisions of pastoral communities as well as a study to be conducted.

37. **Recognition of Customary Land Administration and Use Systems**

1/ Regional laws shall recognize customary institutions; customary land use and management practices, and conflict resolution mechanisms and shall provide support and follow-up.

2/ Customary land use and management rules and conflict resolution mechanisms shall be of no effect where they contravene the fundamental constitutional rights, women rights, as well as the rights and obligations provided by other laws.

38. **Leasing Communal Holding**

1/ Pastoralists may Lease out part of their communal land holdings based on their

ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡ የጋራ ውሳኔው ከተጠቃሚዎች ቢያንስ በሶስት አራተኛው ድምፅ መወሰን አለበት

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የወል መሬት ሲከራይ የተጠቃሚውን የግጦሽ መሬት በማያሳጣ መልኩ መሆን አለበት፡፡

፫/ የአርብቶ አደር አካባቢ የገጠር መሬት አስተዳደር ተቋማት በክልል፣ በዞን፣ በልዩወረዳ፣ ከተማ እና በወረዳ ጽህፈት ቤታቸው በኩል ከባህላዊ የማህበረሰቡ መሪዎች ጋር በመሆን የሚከራይ የወል መሬት መለየት፣ የወል መሬት ለመከራየት የሚፈልጉ ተጠቃሚዎችን እየመዘገበ የሚያገናኝ እና የአካባቢውን የመሬት ኪራይ ገበያ እያጠና ለአከራይና ተከራይ መረጃ የሚሰጥ ክፍል ያቋቁማሉ፡፡

## ፴፱. ከወል መሬት የሚገኝ ገቢ አስተዳደር

፩/ ከወል መሬት የሚገኝ ገቢ ከኪራይ፣ ከካሳ ክፍያ፣ ከመሬቱ የሚገኝ ማንኛውም ምርት ሽያጭ እና ሌሎችንም ያጠቃልላል፡፡

፪/ ከወል መሬት ከሚገኘው ገቢ ሁሉንም ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርግ የወል መሬት ይዞታ ተጠቃሚዎች ፈንድ በክልሎች መቋቋም አለበት፡፡

፫/ በፈንዱ የኢኮኖሚ አቅም የሌላቸው ሴቶች እና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ሰዎችን አዎንታዊ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው::

## ንዑስ ክፍል ፯
## በገጠር መሬት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን ስለመፍታት

## ፵. በገጠር መሬት ላይ የሚነሱ ክርክሮች የሚፈቱበት አግባብ

፩/ በገጠር መሬት ላይ ተበደልሁ የሚል ወገን ጉዳዩን ከተከራካሪ ጋር በስምምነት ወይም እራሳቸው በሚመርጧቸው አስማሚ ሽማግሌዎች አማካኝነት መፍታት፣ ወይም ስልጣን ላለው የክልል ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ ጉዳዩ እንዲታይለት ማድረግ ይችላል፡፡

፪/ ስልጣን ያለው የክልል ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል፡፡

፫/ ከሽምግልናና ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ በሌላ አካል የመሬት ክርክር መታየት የለበትም፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተደነገገው ቢኖርም የአስተዳደር አካላት በመሬት ጉዳይ በሕግ በተሰጣቸው ተግባራት ላይ

common decision. The decision shall be supported by at least three-fourth majority vote of the user community.

2/ Where communal land is leased out pursuant to Sub-Article (1) of this Article, it shall not result in the deprivation of their grazing land.

3/ Regional Rural Land Administration Institutions shall establish working teams in their Regional, Zone, Special Woreda, City, Woreda, and Kebele offices that may gather and provide information about potential lessors and lessees as well as jointly develop their holdings with investors. Such working teams shall conduct assessments on the local land market, and avail information to interested parties.

## 39. Communal Land Income Management

1/ Income from communal land includes rent, compensation, sales of any produce from the land, and others.

2/ A communal land users' fund shall be established by regions, with the income generated from the communal land, for the benefit the entire community.

3/ The fund shall provide affirmative support to economically disadvantaged women and vulnerable groups.

## SECTION SEVEN
## RURAL LAND DISPUTE RESOLUTION

## 40. Jurisdiction on Rural Land Disputes

1/ Rural land disputes may be solved through negotiation, mediation/ conciliation, or adjudicated in the regular court having jurisdiction.

2/ A decision of the regional court having jurisdiction may be taken by appeal.

3/ Such bodies other than mediators and regular courts may not see land disputes.

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (3) of this Article, Administrative bodies shall not be prevented from

የሚነሱ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ከማየት የሚከለክል አይደለም፡፡

**፵፩. ሴቶችና ድጋፍ የሚሹ ሰዎችን ወክሎ ስለመከራከር**

፩/ በሌሎች ሕጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ለመከራከር የገንዘብ አቅም የሌላቸውን ሴቶች እና ድጋፍ የሚሹ ሰዎችን በመሬት የመጠቀም መብት ለማስከበር የሴቶች፣ ህጻናትና የማህበራዊ ጉዳይ ተቋማት እነርሱን ወክለው ሊከራከሩ ይችላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሱትን ሰዎች በመወከል የሚከራከሩ ተቋማትን በተመለከተ ፍትህ ሚኒስቴር ወይም ፍትህ ቢሮ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የገጠር መሬት ምዝገባና ቅየሳ

### ንዑስ ክፍል ፩

### የገጠር መሬት ምዝገባና ቅየሳ ተቋም

**፵፪. መቋቋም**

፩/ የክልል መንግስታት የገጠር መሬት ምዝገባና ቅየሳ ክፍሎችን በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋማት ስር ያቋቁማሉ፡፡

፪/ የክፍሎቹ አደረጃጀት ስልጣንና ኃላፊነት በክልል መንግስታት ሕጎች ይወሰናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የገጠር መሬት ምዝገባና ቅየሳ ክፍሎች በክልል፣ በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ ከተማ እና በወረዳ ደረጃ ይደራጃሉ፡፡

፬/ የክልል የገጠር መሬት ምዝገባና ቅየሳ ክፍሎች በዋና መዝጋቢና ቀያሽ፣ የዞን፣ የልዩ ወረዳ እና የከተማ የገጠር መሬት ምዝገባና ቅየሳ ክፍሎች በመዝጋቢና ቀያሽ ፤ የወረዳ የገጠር መሬት ምዝገባና ቅየሳ ክፍሎች ደግሞ በወረዳ መዝጋቢና ቀያሽ ይመራሉ፡፡

፭/ የክልል ዋናው መዝጋቢና ዋናው ቀያሽ እንዲሁም የወረዳው መዝጋቢና የወረዳው ቀያሽ በክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋም ይመደባሉ፡፡

entertaining administrative issues that arise from land matters within their mandates.

**41. Representing Women and Other Vulnerable Groups**

1/ Without prejudice to the provisions provided in other laws, women, children and social affairs' institutions may represent poor women and vulnerable groups in a court of law to protect their land right.

2/ The Ministry of Justice or the Bureau of Justice shall develop a procedural system regarding institutions that are mandated to represent persons mentioned in Sub-Article (1) of this Article

## PART THREE

## RURAL LAND REGISTRATION AND SURVEYING

### SECTION ONE

### RURAL LAND REGISTRATION AND SURVEYING INSTITUTION

**42. Establishment**

1/ Rural land registration and surveying departments shall be established by regional governments under their Rural Land Administration and UseInstitutions.

2/ The organizational structure; and powers and responsibilities of the departments shall be determined under regional laws.

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, rural land registration and surveying departments shall be established at Regional, Zone, Special Woreda, City, and Woreda levels.

4/ Regional rural land registration and surveying departments shall be led by the chief registrar and chief surveyor; zonal, special woreda and urban rural land registration and survey units by registrar and surveyor; while woreda land registration and surveying departments shall be led by woreda registrar and surveyor.

5/ The Regional Chief Registrar and Chief Surveyor; and the Woreda Registrar and Surveyor shall be appointed by Regional Governments.

፮/ የክልል የዋናው መዝጋቢና ዋናው ቀያሽ እንዲሁም የወረዳው መዝጋቢና የወረዳው ቀያሽ ስልጣንና ተግባር በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች ይወሰናል፡፡ ተጠሪነታቸውም ለሚመለከተው ተቋም ኃላፊ ይሆናል፡፡

**፵፫. <u>የገጠር መሬት ይዞታ የምዝገባና ቅየሳ ሥርዓት</u>**

፩/ የገጠር መሬት ይዞታን የማረጋገጥ ሂደት አስገዳጅና ሥርዓታዊ በአንድ አካባቢ ያሉ ማሳዎችን በአንድ ወቅት በተርታ በመለካትና በመመዝገብ የሚከናወን ይሆናል፡፡

፪/ የምዝገባ ሥርዓቱ ማሣን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

**፵፬. <u>ልዩ የማሣ መለያ ቁጥር አሰጣጥ</u>**

፩/ ልዩ የማሳ መለያ ቁጥር የሚሰጠው አስተዳደራዊ መዋቅርን መሠረት በማድረግ ከላይ ወደ ታች ሆኖ የሚከተሉትን ባህሪያት ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) ለአንድ ማሳ የተሰጠ ልዩ የማሳ መለያ ቁጥር ለሌላ መሰጠት የለበትም፤

ለ) ይዞታ በሚከፈልበትና በሚዋሀድበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር የይዞታ ልውውጥና ይዞታን ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው በሚተላለፍበት ጊዜ ሁሉ የማይለዋወጥ ቋሚ መሆን ይኖርበታል፡፡

፪/ ልዩ የማሳ መለያ ቁጥር የሚከተሉትን ይይዛል፡-

ሀ) የክልሉ መለያ በፊደል ሆኖ ሁለት ሆሄያት ያሉት፣

ለ) የዞን መለያ በቁጥር ሆኖ ሁለት አሃዝ ያሉት፣

ሐ) የወረዳ መለያ በቁጥር ሆኖ ሁለት አሃዝ ያሉት፣

መ) የቀበሌ መለያ በቁጥር ሆኖ ሦስት አሃዝ ያሉት፣ እና

ሠ) የማሳ መለያ በቁጥር ሆኖ አምስት አሃዝ ያሉት፣

ይሆናል፡፡

**፵፭. <u>ብሔራዊ የጂኦዴቲክ መነሻ ነጥቦች ገዥ ስለመሆናቸው</u>**

የተለያዩ የገጠር ካዳስተር ቅየሳ ዘዴዎች ከብሔራዊ የጂኦዴቲክ መነሻ ነጥቦች ጋር መተሳሰር አለበት፡፡

6/ The powers and responsibilities of the Regional Chief Registrar and Chief Surveyor; and the Woreda Registrar and Surveyor shall be determined under regional laws. They shall be accountable to the respective institution head.

**43. <u>Rural Land Registration and Surveying Procedure</u>**

1/ The rural land adjudication system shall be compulsory and systematic.

2/ The registration system shall be parcel based.

**44. <u>Unique Parcel Identification Number</u>**

1/ The assignment of unique parcel identification number shall be given in order of descending government administrative structure and shall fulfill the following features:

a) A unique parcel identification number that has been assigned to a parcel may not be given to another parcel;

b) It shall remain permanent even during the exchange and transfer of holdings; except in cases of division and amalgamation of holdings.

2/ The unique parcel identification number shall contain:

a) The regional identification that shall be represented by two letters;

b) The zonal identification that shall be represented by two numbers;

c) The woreda identification that shall be represented by two numbers;

d) The kebele identification that shall be represented by three numbers;

e) The parcel identification that shall be represented by five numbers.

**45. <u>National Geodetic Ground Control Points</u>**

The different rural cadastral surveying methods shall be networked with the national geodetic ground control points.

**፵፮. <u>አሳታፊ የገጠር መሬት ይዞታ ምዝገባ</u>**

የገጠር መሬት ይዞታ ምዝገባ ህብረተሰቡን ያሳተፈ መሆን አለበት፡፡

**፵፯. <u>የሕጻናትን፣ የሴቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችንና በአካባቢው ያልተገኙ ሰዎችን መብት ስለመጠበቅ</u>**

፩/ የክልል መንግስታት የሚያወጧቸው ሕጎች የገጠር መሬት ይዞታን በማረጋገጥ ሂደት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በአካባቢው ያልተገኙ ሰዎችን መብት የሚያስጠብቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

፪/ በተለይ የሕጻናት፣ አካል ጉዳተኞች እንዲሁም የሴቶች ይዞታ በሚረጋገጥበት ቦታ እና ጊዜ ባለመገኘታቸው መብታቸውን እንዳያጡ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፫/ ወኪል ወይም ሞግዚት ነኝ ባይ ይዞታን ለማረጋገጥ ወይም ለማስመዝገብ በሚቀርብበት ጊዜ መዝጋቢ አካላት ሕጋዊ ውክልናቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

**፵፰. <u>በይዞታ ማረጋገጫ መረጃ ላይ ተቃውሞ ስለማቅረብና ማሻሻያ ስለማድረግ</u>**

፩/ የገጠር መሬት ይዞታን በተመለከተ የተያዘ መረጃ የመጨረሻ ሆኖ በገጠር መሬት መዝገብ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታ የሚያቀርብበት የጊዜ ገደብና ሥነ-ሥርዓት በክልል መንግስታት ይወሰናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚወሰነው ጊዜ ከ ስድስት ወር ያነሰ ሊሆን አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገው ጊዜ ካለፈ በኋላ ማንኛውም ባለ ይዞታ ስለተመዘገበው መረጃ ያውቃል ተብሎ ይገመታል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ስለምዝገባ መረጃው አላውቅም የሚል መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡

**፵፱. <u>ስለ የባህር መዝገብ</u>**

የገጠር መሬት ምዝገባ መረጃዎች በባህር መዝገብ ውስጥ መያዝ አለባቸው፡፡

**፶. <u>ስለ ዲጂታል የመረጃ ሥርዓት</u>**

፩/ በባህር መዝገብ የሰፈሩ መረጃዎች ወደ ዲጂታል የመረጃ ሥርዓት መሸጋገር አለባቸው፡፡

**46. <u>Participatory Registration Process</u>**

The rural landholding registration shall be participatory.

**47. <u>Protecting the Rights of Children, Women, Disabled and Absentee Landholders</u>**

1/ Regional States shall ensure that the laws they enacted protect the rights of landholders who may not be present during the rural land adjudication process for reasons beyond their control.

2/ Special emphasis shall be given to the protection of rights of children; people with disabilities; and women who may not be present at the time and place of adjudication of rights.

3/ Registering organs shall ensure that representatives or tutors who appear during adjudication processes or registration of holding rights have produced their power of attorney.

**48. <u>Objections to the Adjudication Information and Request for Amendment</u>**

1/ Regional States shall determine the time limit and procedure where aggrieved parties may lodge objections and apply for rectification of the adjudication information before the information pertaining to rural land holding is entered into the rural land register.

2/ The time limit to be determined as per Sub- Article (1) of this Article may not be less than six month.

3/ After the lapse of the time limit provided under Sub-Article (2) of this Article, every land holder is presumed to be aware of the registered information. objection based on lack of knowledge of registration is not acceptable.

**49. <u>Registry Book</u>**

Rural land registration information shall be contained in the registry book.

**50. <u>Digital Land Information System</u>**

1/ Information contained in the registry book shall be migrated to the digital land information system.

፪/ በመሬት ይዞታ ላይ የሚደረጉ የመብት ማስተላለፍና ገደቦች በዲጂታል የመረጃ ሥርዓቱ መመዝገብ አለባቸው፡፡

፫/ የሰነድ መዛግብት እና የዲጂታል የመረጃ ሥርዓት እንደ አግባብነቱ ለማስረጃነት ያገለግላሉ፡፡

## ፶፩. ስለ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

፩/ የገጠር መሬት ባለ ይዞታ በይዞታው ስር ለሚገኘው እያንዳንዱ ማሣ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መሰጠት አለበት፡፡

፪/ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሚስጥራዊ ኮድ ሊኖረው ይችላል፡፡

## ፶፪. የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ውጤት

፩/ አንድ ማሣ በአንድ ባለ ይዞታ ስም ተመዝግቦ የምስክር ወረቀት ከተሰጠው የምስክር ወረቀቱ ማንኛውንም የባለይዞታነት መብትና ጥቅም ከነግዴታዎቹ ያስገኝለታል፡፡

፪/ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለይዞታነትን የማረጋገጫ የመጨረሻ ማስረጃ ነው፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ላይ ማንኛውም ተቃራኒ ማስረጃ አይቀርብበትም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም በይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ላይ መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው፡-

ሀ) ምዝገባው ሥልጣን በሌለው አካል ተካሂዶ የነበረ ከሆነ፣ ወይም

ለ) ምዝገባው ሕገ ወጥ በሆነ ሰነድ ላይ ተመርኩዞ የተከናወነ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ የገጠር መሬት የመመዝገብ ሥልጠን የተሰጠው መዝጋቢ አካል በምዝገባ ሂደት በፈፀመው ስህተት ጉዳት የደረሰበት ባለይዞታ ለደረሰበት ጉዳት በመዝጋቢው አካል ተመጣጣኝ ካሣ ይከፈለዋል፡፡

## ፶፫. የምዝገባ መረጃን ወቅታዊ ስለማድረግ

፩/ የባለ ይዞታ ለውጥ በተደረገ ጊዜ፣ ማሳ በተከፋፈለ ወይም በተዋሃደ ጊዜ ሁሉ የመሬት ምዝገባ ሰነዱ መሻሻል ይኖርበታል፡፡

፪/ ሌሎች ከመሬት ይዞታ ጋር የተያያዙ ገደቦችና እገዳዎች ሊመዘገቡ ይገባል፡፡

## ፶፬. አገር አቀፍ የገጠር መሬት መረጃ ሥርዓት

፩/ በፌደራል ደረጃ የገጠር መሬት የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

2/ All land rights transfers and restrictions shall be registered in the digital land information system.

3/ Printed documents and digital land information systems may be used as evidence, as relevant.

## 51. Landholding Certificate

1/ Rural landholders shall be issued with a landholding certificate for each of their parcels.

2/ The landholding certificates may carry secret codes.

## 52. Effect of Landholding Certificate

1/ A landholder shall have all the rights and duties that a holding right confers over the parcel that is registered and certified in his name.

2/ Landholding certificate is the ultimate evidence that proves a landholder. Contrary evidence may not be admitted to disprove the landholding certificate.

3/ Objections over rights accrued under Sub-Articles (1) and (2) of this Article may only be made where:

a) The registration was conducted by an unauthorized organ; or

b) The registration was made based on an unlawful document.

4/ A landholder who suffered damage due to mistakes committed by a rural land registering officer or organ authorized under this Proclamation, shall be entitled to commensurate compensation.

## 53. Updating the Register

1/ The land information shall be updated during the change of landholders; division; or amalgamation of parcels.

2/ All other restrictions on landholding rights shall be registered.

## 54. National Rural Land Information System

1/ National Rural Land Information System shall be established at federal level.

፪/ ሚኒስቴሩ የገጠር መሬት የመረጃ ሥርዓትን ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፡፡

**፶፭. <u>የመሬት መረጃ ልውውጥና ቅንጅት</u>**

፩/ የክልል የገጠር መሬት የመረጃ ሥርዓት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስቴሩ ከሚቋቋመው የፌደራል የገጠር መሬት የመረጃ ሥርዓት ጋር የተገናኘና የተቀናጀ መሆን ይኖርበታል፡፡

፪/ ከክልል ወደ ፌደራል የመረጃ ሥርዓት መላክ የሚገባው የገጠር መሬት መረጃ ዓይነትና ይዘት በሚኒስቴሩ ይወሰናል፡፡

፫/ ክልሎች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ሚኒስቴሩ በሚወስነው አግባብ ወቅታዊ መረጃዎችን ለፌደራል የመረጃ ሥርዓት መላክ አለባቸው፡፡

**፶፮. <u>ባይመዘገቡም የሕግ ውጤት ስላላቸው መብቶች</u>**

ባለይዞታው ባስመዘገበው ይዞታ ላይ እንደ ዕዳ ወይም ገደብ ባይመዘገቡም የሚከተሉት ገደቦች ተቀባይነት አላቸው፡-

፩/ በክልል የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ በባህር መዝገቡ ላይ እንዲመዘገቡ ግዴታ ያልተጣለባቸው እንደ አጭር ጊዜ የኪራይ ውሎች፣ የጋራ እርሻ ስምምነቶች ወይም ጊዜያዊ የጋራ ይዞታ ስምምነቶች፣ ወይም

፪/ በተመዘገበው ይዞታ ላይ የተቋቋመውን መብት የሚቀንሱ ወይም የሚያሳጡ እንደ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ወይም የከተማ ፕላን ወይም ተመሳሳይ በፌደራል ወይም በክልል ሕግ መሠረት የሚቋቋሙ ግዴታዎች፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ፪</u>**

**<u>ስለ መረጃ የማግኘት መብትና ስለ ክፍያ</u>**

**፶፯. <u>መረጃ የማግኘት መብት</u>**

፩/ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋማት ማናቸውንም የምዝገባ ሰነዶች ጥቅም አለን ለሚሉ ወገኖች ክፍት ማድረግ አለባቸው፡፡

፪/ የመሬት ይዞታ መረጃዎችን ለሚፈልጉ ጠያቂዎች የሚሰጠው መረጃ ዓይነት፣ የሚሰጥበት ሥርዓትና የሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ መጠን በየክልሉ በሚወጡ ሕጎች ይወሰናል፡፡

2/ The Ministry shall organize and administer the rural land information system.

**55. <u>Coordination and Sharing of Land Information</u>**

1/ Regional rural land information system shall be linked and harmonized with the federal rural land information system which is established under this Proclamation.

2/ The type and content of rural land information that need to be sent from regional to federal land information system shall be determined by the Ministry.

3/ Regional States shall send updated information to the federal land information system pursuant to Sub-Article (2) of this Article.

**56. <u>Unregistered Valid Rights</u>**

Even if not registered as debt or restriction over the registered holding, the following restrictions shall have legal effect:

1/ As short-term lease; sharecropping; or short-term joint holding contracts which are not required to be recorded in the land register under regional land administration law,

2/ Such obligations established by federal or regional laws as public health; urban plans; or similar servitudes which restrict; or totally cancel the rights created on registered holdings.

**<u>SECTION TWO</u>**

**<u>RIGHT TO ACCESS INFORMATION AND PAYMENT</u>**

**57. <u>Right to Access to Information</u>**

1/ Rural Land Administration and Use Institutions shall avail registration information to all interested parties.

2/ The type of information, and procedure of accessing and availing the information and the corresponding service fees to be paid shall be determined by regional laws.

**፶፰. ስለ ክፍያ**

፩/ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚደረግ ምዝገባና ቅየሳ ክፍያ አይጠየቅም፡፡

፪/ የይዞታ መረጃን ወቅታዊ ለማድረግ ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ መከፈል አለበት፡፡

፫/ ይዞታን ኩታ ገጠም የማድረግ ውጤት ያለው የይዞታ ልውውጥ በሚደረግበት ጊዜ ተለዋዋጮቹ ከክፍያ ነፃ ይሆናሉ፡፡

## ንዑስ ክፍል ፫

## የአስፈፃሚ አካላት ኃላፊነት

**፶፱. የሚኒስቴሩ ኃላፊነት**

ሚኒስቴሩ፡-

፩/ የሚመለከታቸውን ተቋማት በማስተባበርና የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይህን አዋጅ የማስፈፀም፤

፪/ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያግዙና ለመረጃ ተናባቢነት የሚረዱ አገር አቀፍ ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፤ እንዲሁም

፫/ አገር አቀፍ የገጠር መሬት የመረጃ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡

**፷. የክልሎች ኃላፊነት**

፩/ እንደ ክልሉ ነባራዊ ሁኔታ የገጠር መሬትን የሚያስተዳድር አደረጃጀት ያቋቁማሉ፡፡

፪/ ከዚህ ሕግ ጋር የሚጣጣም ዝርዝር ሕግ በማውጣት ይህንን አዋጅ የማስፈፀም ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፫/ የሴቶችና ድጋፍ የሚሹ ሰዎች የገጠር መሬት የመጠቀም መብትን በክልሉ ባሉ ተቋማት ተፈፃሚ መሆናቸውን የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**፷፩. የክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋም ኃላፊነት**

፩/ የክልል የገጠር መሬት አስተዳደር ተቋማት የገጠር መሬት ወደ ከተማ ክልል ሲካተትና ከመካተቱ በፊት እንዲሁም የገጠር መሬት ለሌላ አገልግሎት እንዲውል ሲደረግ ሂደቱን ወይም ሽግግሩን እስከ መጨረሻው ሊመሩ ይገባል፡፡

፪/ የክልል መንግስታት በተለይም ደግሞ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋማት የአርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ይዞታ ወደ ከተማ ክልል

**58. Payment**

1/ No payment shall be requested for initial registration and surveying.

2/ Service fees shall be paid for updating landholding data.

3/ Service fees may not be paid in cases of land exchange which has the effect of land consolidation.

## SECTION THREE

## RESPONSIBILITIES OF EXECUTIVE ORGANS

**59. The Responsibility of the Ministry**

The Ministry shall be responsible to:

1/ Ensure implementation of this Proclamation by coordinating and providing the necessary professional support to relevant institutions;

2/ Prepare national standards to implement this Proclamation and ensure harmonization of the land information systems; and

3/ Facilitate the establishment of national rural land information system.

**60. The Responsibility of Regions**

1/ Based on their reality, regions shall establish rural land administration and use institutions.

2/ Regions shall issue detailed laws in conformity with this Proclamation.

3/ Regional States shall be responsible to oversee the implementation of the rules on the land rights of women and vulnerable group by various regional institutions.

**61. Responsibility of Regional Rural Land Administration and Use Institutions**

1/ Regional Rural Land Administration and Use Institutions shall lead the process where rural land is expropriated for urban expansion or for other purposes.

2/ In the event of expropriation of farmers' and pastoralists' land for urban expansion, Regional Governments, especially Rural Land Administration

ሲካተት አስቀድሞ ካሣ ሳይከፈል የመጠቀምና የይዞታ መብታቸው እንዳይቋረጥ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፷፪. የወንጀል ተጠያቂነት

፩/ ማንኛውም ሰው የግል፣ የወል ወይም የመንግሥት ይዞታን በሕገወጥ መንገድ የወረረ ከብር ፴ሺ. እስከ ፩፻ሺ. ወይም ከ፩ ዓመት እስከ ፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በግል፣ በወል ወይም በመንግሥት ይዞታ ላይ ጉዳት ያደረሰ ከብር ፶ሺ. እስከ ፩፻፶ሺ. ወይም ከ፫ ዓመት እስከ ፯ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

፫/ ማንኛውም ሰው ባልተፈቀደ ቦታ ላይ ማንኛውንም ግንባታ የሰራ ወይም እንዲሰራ የፈቀደ ከብር ፳፭ሺ. እስከ ፶ሺ. ወይም ከ፩ ዓመት እስከ ፫ ዓመት በሚደርስ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

፬/ ማንኛውም ሰው ከመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ውጪ ይዞታውን ጥቅም ላይ ካዋለ ከብር ፳ሺ. እስከ ፶ሺ. ወይም ከ፩ ዓመት እስከ ፫ ዓመት በሚደርስ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

፭/ ሀሰተኛ የመሬት ይዞታ ማስረጃ ያቀረበ ባለይዞታ፣ ማስረጃ የሰወረ ወይም የተሳሳተ ማስረጃ የሰጠ ባለሙያ ከብር ፲ሺ. እስከ ፳፭ሺ. ወይም ከ፩ ዓመት እስከ ፫ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

፮/ ማንኛውም ሰው መሬት የሸጠ ወይም የገዛ እንደሆነ ከብር ፩፻ሺ. እስከ ፪፻ሺ. ወይም ከ፩ ዓመት እስከ ፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

### ፷፫. የፍትሐ ብሔር ሕጉ አግባብነት

ከዚህ ሕግ ጋር አግባብነት ያላቸውና በዚህ ሕግ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

### ፷፬. ይርጋ

፩/ የመንግስት ወይም የወል ይዞታን በሕገ ወጥ መንገድ የያዘ ሰው ይርጋን እንደ መከላከያ ሊያነሳ አይችልም፡፡

and Use Institutions, shall ensure that no use and holding right be taken before compensation is paid in advance.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 62. Criminal Liability

1/ Any person who illegally invades private, communal or state holdings shall be fined with payment of 30,000 to 100,000 Birr or punished with 1 to 5 years' rigorous imprisonment or both.

2/ Any person who causes damage to private, communal or state holding shall be fined with payment of 50,000 to 150,000 Birr or punished with 3 to 7 years rigorous imprisonment or both.

3/ Any person who constructs or permits any construction in an unauthorized place shall be fined with payment of 25,000 to 50,000 Birr or punished with 1 to 3 years imprisonment or both.

4/ Any person who uses his holding contrary to the land use plan shall be fined with payment of 20,000 to 50,000 Birr or punished with 1 to 3 years imprisonment or both.

5/ A landholder who submits a forged landholding certificate, a professional who hides evidence or gives false evidence shall be fined with payment of 10,000 to 25,000 Birr or punished with 1 to 3 years rigorous imprisonment or both.

6/ Anyone who sells or buys land shall be fined with payment of 100,000 to 200,000 Birr or punished with 1 to 5 years of rigorous imprisonment or both.

### 63. Application of the Civil Code

The Civil Code provisions shall apply as deemed necessary in areas relevant to this law that are not covered under this Proclamation.

### 64. Period of Limitation

1/ A person who illegally possesses state or communal holding may not invoke a period of limitation as a defense.

፪/ ይዞታዬ ያለአግባብ በሌላ ሰው ተወስዶብኛል የሚል ሰው መብቱን መጠየቅ ከነበረበት ወይም ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ፲፭ ዓመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ መብቱ በይርጋ ይታገዳል፡፡

፫/ ሌሎች መብትን ለመጠየቅ በሌሎች ሕጎች የተቀመጡት የይርጋ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ፷፭. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

፩/ የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች ይህ አዋጅ ከመፅደቁ በፊት በክልልና በፌደራል የዳኝነት አካላት ፊት ቀርበው ክርክር እየተደረገባቸው ባሉ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡

፪/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተሰጡ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች ተቀባይነት አላቸው፡፡

## ፷፮. <u>ደንብ የማውጣት ስልጣን</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት እንደ አስፈላጊነቱ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፷፯. <u>ስለተሻሩና ተፈፃሚ ስለማይሆኑ ሕጎች</u>

፩/ የፌደራል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፬፻፶፮/፲፱፻፺፯ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፷፰. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፰ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ፕሬዚዳንት**

2/ An action to reclaim a holding which was illegally possessed by another person shall be barred by period of limitation if not brought within 15 years after the date he should have brought the case or having become aware of his rights.

3/ Period of limitation provided in other laws shall apply in respect of claims of other rights.

## 65. <u>Transitory Provisions</u>

1/ The provisions of this Proclamation may not apply to cases that are pending at federal or regional judicial bodies before the coming into force of this Proclamation.

2/ Landholding certificates, which were issued before the coming in to force of this Proclamation shall be valid.

## 66. <u>Power to Issue Regulation</u>

The Council of Ministers may issue Regulations to implement this Proclamation.

## 67. <u>Repeals</u>

1/ The Federal Rural Land Administration and Use Proclamation No 456/2005 is hereby repealed.

2/ No law, Regulation, Directive or Practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for in this Proclamation.

## 68. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, on this 14th day of August, 2024**

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**